የኮ/መ/ቁ 291672

ጥር 30 ቀን 2014 ዓ.ም

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት

የልደታ ምድብ 17ኛ ባንክና አንሹራንስ ችሎት

## ዳኛ:- መካ ነስሩ

ከሳሽ - አቶ ገረመው ሰሊቶ - ጠበቃ ኤርሚስ ብርሀኑ ቀረቡ

ተከሳሽ- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቴዎድሮስ አደባባይ ቅርንጫፍ -ነ/ፈጅ ለገሰ ኃይሌ ቀረቡ

ጣልቃ ገብ- አቶ ሃይሉ በቀለ- በሌሉበት

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍ ር ድ

የከሳሽ ጠበቃ መጋቢት 28 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ የክስ አቤቱታ ከሳሽ ተከሳሽ ጋር ካለው የባንክ ሂሳብ ሂሳብ ቁጥር 1000272969314 በቼክ ቁጥር ሲዲ306903639 ብር 320000 (ሶስት መቶ ሃያ ሺህ) በቀን 20/06/2012 ዓ.ም ከቀኑ 6:27 ላይ በሃስተኛና የከሳሽ ባልሆነ ፊርማ የተወሰደባቸውና ገንዘብ የተቀነሰባቸው ስለሆኑ፣ ተከሳሽ ይህንን ያደረገው ለራሱ ወይም ደግሞ ለሌላ ሶስተኛ ወገኖች ያልተገባ ብልጽግና ለማስገኘት ስለመሆኑ፣ በዚህም ተከሳሽ በራሱም ሆነ በሰራተኛው ጥፋት ያለበት በመሆኑ ከውል እንዲሁም ከውልውጪ በሆነ ሃላፊነት ከሳሽ ያላግባብ ከሂሳብ አካውንቱ የተቀነሰበትን ገንዘብ ከህጋዊ ወለዱ ጋር ሊመልስ ይገባል በማለት ክስ አቅርበዋል። በማስረጃትም የሰው ምስክር በመጥቀስ ሰነዶችን አያይዘዋል።

የተከሳሽ ነገረ ፈጅ ሚያዚያ 29 ቀን 2013 ዓም በተጻፈ የክስ መልስ ተከሳሽ በየካቲት 20 ቀን 2012 ዓ.ም በከሳሽ በተጠቀሰው የቼክ ቁጥርና የገንዘብ መጠን ለአቶ ሃይሉ በቀለ ለተባሉ ግለሰብ ክፍያ የፈጸመ መሆኑን የማይክድ ስለመሆኑ። ይህ ሁን እንጂ ተከሳሽ ክፍያ የፈጸመው የቼኩን ትክክለኛነት፣ የከሳሽ ፊርማ ከቼኩ ላይ ከተፈረመው ፊርማ ጋር በአይን እይታ የሚመሳሰል መሆኑን በማረጋገጥ፣ ቼኩ የተጻፈበት ቀን እንዲሁም

የሚከፈልበትን ቀን በማረጋገጥ እንዲሁም የገንዘቡን መጠን በቁጥርና በአሃዝ በማመሳከር በባንኩ መመሪያና ህግ መሰረት የተደረገ ስለመሆኑ። እንዲሁም ተከሳሽ የቀረበለትንየፊርማ ናሙና በአይን እይታ ከማስተያየት በቀር ፊርማ የመመርመር ልዩ ችሎታ የሌላቸው ስለመሆኑ፣ ተከሳሽ ከከሳሽ ቼኩ ለክፍያ በቀረበበት ወቅት በእጅ ስልካቸው በመደወል ክፍያ እንዲፈጸም ከከሳሹ የይሁንታ ቃላቸውን የተቀበለ ስለመሆኑ ፣ በከሳሽ ቸልተኝነትና ጥፋትነ በሌላ ሰው እጅ ገብተው ለሚከፈሉ የቼክ ክፍያዎች ባንኩ በሃላፊነት ተጠያቂ ሊሆንበት የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣ ከሳሽ በእጃቸው የነበረው ክፍያ ተፈጽሞበታል የተባለው ቼክ ጠፍቶባቸው ወይም ተሰርቆባቸው የነበረ ከሆነም ለተከሳሽ ክፍያ እንዳይፈጽም ያላመለከቱ ስለመሆኑ፣ የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 41535 ቅጽ 12 ላይ ምንም እንኩዋን በተጭበረበረ ቼክ የተከፈለ ቢሆንም እንኳን ባንኮች የተለመደውን አሰራር ተከትለው የሰሩ እስከሆነ ድረስ ሃላፊነት የለባቸውም ተብሎ የተወሰነ ስለመሆኑ በተመሳሳይ መልኩ ተከሳሽ ሃላፊነት ሊኖርበት አይገባም በማለት መልስ ሰጥተዋል።

ጣልቃ ገብ ጥሪ ተደረገላቸው ቢሆንም አልቀረቡም። በዚህም መሰረት ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ በሌሉበት ጉዳዩ እንዲቀጥል አዟል።

ፍርድ ቤቱ በፈሬ ነገር ላይ ክስ ሰምቷል። በዚህም መሰረት ከሳሽ ስልክ ያልተደወለላቸው ስለመሆኑ፣ ምንም እንኳን በብሄራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት ከብር 50000 (ሃምሳ ሺህ) በላይማውጣት የተከለከለ ቢሆንም ከሳሽ ግን አውጥቶ የከፈለ ስለመሆኑ፣ ባንኩ ከውል በመነጨ እንዲሁም ከውል የመነጨ ሃላፊነት የለበትም የሚባል ከሆነ እንኩዋን ከውል ውጪ በሆነ ሃላፊነት ሊጠየቅ ይገባዋል በማለት ክስ አሰምተዋል።

ተከሳሽ በበኩላቸው የፊርማ ናሙናው የማያሻማ የማያከራክርና ተመሳሳይ ስለመሆኑ፣ ፊርማ የመለየት ሳንሳዊ አሰራር የሌላቸው ስለመሆኑ፣ ከ50000 (ሃምሳ ሺህ ብር) በላይ የሚለው መመሪያ 2013 ላይ የወጣ ስለመሆኑ፣ ክፍያ በተፈጸመበት ቀን ስልክ ለደንበኛው የተደወለ ስለመሆኑ፣ ስልኩ የጠራው ደንበናው ጋር ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ማጣራት ተከሳሽ ግዴታ የሌለበት ስለመሆኑ፣ ቼኩ ተፍቷል የሚል ቅሬታ ያልቀረበ እና ክፍያ እንዳይከፈል ቅሬታ ያልቀረበ ስለመሆኑ በመግለጽ ተከራክረዋል።

ፍርድ ቤቱም ተከሳሽ ተገቢውን የባንክ አሰራር በመከተል ለቀረበለት ቼክ ክፍያ ፈጽሙዋል ወይስ አልፈጸመም አልፈጸመም ከተባለስ ከሳሽ ከሂሳብ ቁጥሬ ተቀንሶ ተወስዶብኛል ያለውን ገንዘብ ሊመልስ ይገባል ወይስ አይገባም እንዲሁም ጣልቃ-ገብ ክስ የቀረበበት ገንዘብ ለከሳሽ

የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

በከሳሽ በተከሳሽ መካከል ባለው ክርክር ግራ ቀኙ የቼኩን ትክክለኛነት በተመለከተ አልተካካዱም፡፡ ይህ ይሁን እንጂ ቼኩ ላይ ያለው የከሳሽ ፊርማ በአይን እይታ በባንኩ ሲስተም ላይ ባለው የከሳሽ ፊርማ ጋር ተመሳሳይ ነው ወይስ አይደለም እንዲሁም በእለቱ ለከሳሽ ተደውሏል ወይስ አልተደወለም የሚለው ፍሬ ነገር ላይ ልዩነት አላቸውም፡፡ ይህንንም ፍሬ ነገር ለማረጋገጥ ከሳሽና ተከሳሽ የሰው ምስክር አቅርበዋል፡፡ የተከሳሽ 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ምስክሮች የቀረበውን ቼክ ትክክለኛነት፣ የተከፋዩን መታወቂያ፣ የቼኩ ባለቤት ፊርማ ከሲስተም ላይ እንዲሁም በቼኩ ላይ የተፈረመውን በአይን እይታ በማመሳከርና ተመሳሳይ በመሆኑ የሚከፈለው ገንዘብ ከመቶ ሺህ ብር በላይ በመሆኑ ለከሳሽ በመደወል ከሳሽም ይከፈል የሚል እሺታቸውን የገለጹ በመሆኑ ቼኩ እንዲከፈል ማረጋገጫ በመስጠትና በመፈረም እንዲከፈል የቀረበና በካሽ ለቼክ አምጪ ለሆነው ለጣልቃ-ገብ እንደተከፈለ መስክረዋል፡፡

በተቃራኒው የከሳሽ ምስክሮች የከሳሽ ፊርማ በጓደኝነትና በስራ አጋጣሚ በሚያውቁት መሰረት የከሳሽ ፊርማ በቼኩ ላይ ከተቀመጠው ፊርማ ልዩነት ያለው መሆኑን እንዲሁም በእለቱ ከ 4 እና 5 ሰዓት ጀምሮ ማለትም ከታህሳስ 20 እስከ ታህሳስ 21 ድረስ የከሳሽ ስልክ በተደጋጋሚ ሲደውሉ የማይሰራ የነበረ መሆኑን መስክረዋል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን በሃምሌ 14 ቀን 2012 ዓ.ም በተጻፈ የፎረንሲክ ምርመራ ውጤት በቼክ ቁጥር 30903639 በ17/06/2012 ዓ.ም የተዘጋጀው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቼክ በከሳሽ ያልተፈረመ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በፖሊስ የወንጀል ምርመራ መዝገብ ላይ ከኢትዮ ቴሌኮም መጋቢት 24 ቀን 2012 ዓ.ም በቁጥር ኢት/ህግ/ወ.ክ/215/2020 የከሳሽ ስልክ ቁጥር ማለትም 0911514362 ተዘግቶ ያልነበረ ስለመሆኑ እና በእለቱ ያስተናገዳቸውን ስልኮች ዝርዝር በመጥቀስ ማስረጃ ሰጥቷል፡፡

ፍርድ በቤቱም በቼኩ ላይ የተመለከተው ፊርማ ከሳሽ የባንክ ሂሳብ በተከሳሽ ባንክ ሲከፍቱ ከሰጡት የፊርማ ናሙና አንፃር በተለመደው የባንክ አሰራር በባንክ ሰራተኛ በአይን እይታ ሲረጋገጥ በአግባቡ ተጣርቶ ክፍያ የተፈፀመ መሆን አለመሆኑ ከከሳሽ ባንክ ሰራተኞች በተጨማሪ በቼክ ክፍያ በመፈፀም ልምድ ያላቸው ሰራተኞች ገለልተኛ ከሆኑ ሦስት ባንኮች

ምስክርነት አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘው የከሳሽ የፊርማ ናሙና ቼኩ ላይ ከተገለጸው የፊርማ ናሙና ጋር በማስተያየት ባለሞያዎቹ ሊከፍሉ ይችሉ ነበር ወይስ አይችሉም የሚለውን ፍሬ ነገር ማጣራት እንዲቻል ከሶስት የተለያዩ ባንኮች ማለትም ከህብረት ባንክ ከአባይ ባንክ እንዲሁም ከዳሽን ባንክ ባለሞያዎችን አስቀርቦ ሰምቷል፡፡ በዚህም መሰረት የመጡት ባለሞያዎች የፊርማው ናሙና እና ክፍ ተፈፀመበት ቼኩ እንዲሰጣቸው ከተደረገ በኋላ ቼኩ እነሱ ዘንድ ቢቀርብ ይከፍላሉ ወይስ አይከፍሉም ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ቼኩ ቢቀርብላቸው ፊርማው በአይን እይታ ተመሳሳይ የሆነ በመሆኑ እንከፍላለን በማለት ምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡

በአጠቃላይም ክርክሩን ስንመዝነው በመርህ ደረጃ ማንኛውም ቼክ የቀረበ ሰው ባንኩ እንዲከፍለው የመጠየቅ መብት ያለው ሲሆን ቼኩ የቀረበለት ባንክም ቼኩ ያወጣውን ሰው ፊርማን ጨምሮ ሌሎች መገለጽ የሚገባቸውን ሁኔታዎች ተሟልተው የቀረቡ መሆኑን በማረጋገጥ ቼኩ እንደቀረበለት የመክፈል ሃላፊነት አለበት፡፡ ነገር ግን ባንኩ የሚገባውን ጥንቃቄ ሳያደርግ ክፍያ ፈጽሞ ከተገኘ በተከፈለው ገንዘብ ልክ ለደንበኛው ሃላፊነት ያለበት ነው፡፡ ከተያዘው ጉዳይ አንጻር ስንመዝነው ተከሳሽ የቀረበለትን ቼክ የከፈለው የከሳሽን ፊርማ በአይን እይታ ከሲስተም ላይ ካለው የፊርማ ናሙና ጋር አንድ አይነት መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ነው የሚያስብል ነው፡፡ ይህንንም ሊያስብል የቻለው ከተለያዩ ባንኮች የቀረቡት የባለሞያ ምስክሮች ቼክ እነሱ ዘንድ ቢቀርብ በዓይን እይታ ተመሳሳይ የሆነ በመሆኑ ሊከፍሉ የሚችሉ መሆኑን ያረጋገጡቱ በመሆኑ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ምንም እንኳና ተፈረመ የተባለው ፊርማ ተመሳስሎ የቀረበ ፊርማ መነሻነት መሆኑ በወንጀል ምርመራ የተረጋገጠ ቢሆንም ተከሳሽ መቃወሚያ ሳይቀርብበት በቅን ልቦና እና ለስራ አፈጻጸም በተለመደው አኳያ የከፈለው ክፍያ በመሆኑ እንዲሁም ተከሳሽ ልዩ የፊርማ መመርመሪያ ተጠቅሞ አገልግሎት መስጠት የማይጠበቅበት በመሆኑ በንግድ ህግ ቁጥር 861 መሰረት በአግባቡ ሃላፊነቱን ተወጥቷል የሚያስብለው ነው፡፡ በዚሁ ጉዳይ ላይም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 194164 ላይ ተመሳሳይ ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡

ከሳሽ ክፍያው በተፈፀመበት ዕለት ስልካቸው እየሰራ ስላልነበር ስልክ አልተደወለልኝም ነበር ብለው ያቀረቡትንም መከራከሪያ በተመለከተ ከኢትዮ ቴሌኮም የቀረበው ማስረጃ በወቅቱ የከሳሽ ስልክ አገልግሎት ይሰጥ የነበረ መሆኑ ያረጋግጣል፡፡የከሳሽ ስልክ ክፍያ በሚፈፀምበት ወቅት ተደውሎ ማረጋገጫ የሰጡ መሆኑም በተከሳሽ ምስክሮች የተረጋገጠ ፍሬ-ነገር ሲሆን ስልኩም ጥሪዎችን ሲቀበል እንደነበረ ፖሊስ ከኢትዮ ቴሌኮም ያስቀረበው ምላሽ ያስረዳል፡፡

በመሆኑ እንዱም ከሳሽ በተቃራኒው ስልካቸው በተለይ ያልሰራበትን ወይም አገልግሎት ውጪ የነበረ መሆኑን በማስረጃ በማስደገፍ ያላስረዱ በመሆኑ ጥያቄያቸውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

ጣልቃ-ገብ ክስ የቀረበበት ገንዘብ ለከሳሽ የመክፈል ኃላፊነት ያለባቸው መሆን አለመሆኑን በተመለከተ የተያዘው ጭብጥ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ አንድ ቼክ ለባንክ ቀርቦ ክፍያ ሊፈፀምበት የሚገባው በቼክ አውጪው አልያም በቼኩ ላይ ለመፈረም ውክልና የተሰጠው ሰው ሲፈረምበት እንደሆነ በንግድ ህጉ የተመለከተ ሲሆን ለግራ ቀኙ ክርክር ምክንያት የሆነው ቼክ በተከሳሽ ባንክ ቀርቦ ክፍያ የተፈፀመበት የከሳሽ ያልሆነ ፊርማ ተመሳስሎ ተፈርሞበት መሆኑ በክርክር ሂደት የተረጋገጠ ፍሬ-ነገር ነው፡፡

ጣልቃ ገብ በከሳሽ ለቀረበው ክስ እንዲሁም በተከሳሽ ለቀረበው መልስ ቀርበው መልስ አልሰጡም አልተከራከሩም እንዲሁም ሃላፊነት ሊኖርባቸው የማይችልበት ምክንያት ያለ እንደሆነ አላስረዱም፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ከሳሽ እንዲሁም ተከሳሽ ባቀረቧቸው ክርክሮች መሰረት በቀረበ ማስረጃ መሰረት የከሳሽ ቼክ ለባንክ ቀርቦ የተመነዘረው ተመሳስሎ በቀረበ ፊርማ መነሻነት መሆኑን በተለይ በፖሊስ የቀረበው የምርመራ መዝገብ ያስረዳል፡፡ ጣልቃ-ገብ ከከሳሽ በተሠጣቸው ቼክ ከተከሳሽ ባንክ ገንዘብ ወጪ ሊያደርጉ የሚችሉት ከሳሽ ራሳቸው በቼኩ ላይ ፈርመው ሲሰጧቸው ብቻ ቢሆንም በቼኩ ላይ የከሳሽ ፊርማ ያልሆነ ፊርማ ተፈርሞበት ቼኩ ለባንክ ቀርቦ ክፍያ የተፈፀመላቸው በመሆኑ ያለአግባብ ቼኩ ማሟላት ያለበትን ነገር ሳያሟላ ከከሳሽ የባንክ ሂሳብ ባንኩን አታለው ወጪ ያደረጉት ገንዘብ ለከሳሽ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. ተከሳሽ ተገቢውን የባንክ አሰራር በመከተል ለቀረበላቸው ቼክ ክፍያ የፈጸሙ በመሆኑ ከሳሽ ላቀረበው ክስ ኃላፊነት የለባቸውም ተብሎ ተወስኗል፡፡
2. ጣልቃ ገብ ክስ የቀረበበት ገንዘብ ብር 320,000 (ሶስት መቶ ሃያ ሺህ) ክስ ከተመሰረተበት መጋቢት 29 ቀን 2013 ዓ/ም ጀምሮ ተከፍሎ እስኪጠናቀቅ ድረስ ከሚታሰብ 9% ህጋዊ ወለድ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡
3. በዚህ ችሎት በቀረበው ክስ ምክንያት የወጣውን ወጪና የደረሰ ኪሳራ በተመለከተ ለዳንነት ብር 6,050፣ የቴምብር ቀረጥ በማስረጃ ላይ ለማስለጠፍ ብር 10፣ የጋዜጣ ጥሪ ማድረጊያ ብር 461 እንዲሁም የጠበቃ አበል በጥብቅና አገልግሎት ውሉ ላይ

የተመከተው ገንዘብ መተን ብር 80,000 የተጋነነ በመሆኑ ጉዳዩ ከወሰደው ጊዜ እና ውስብስብነት አንፃር በማገናዘብ ክስ በቀረበበት ገንዘብ መጠን አስር በመቶ ብር 32,000 በድምሩ ብር 38,521 (ሰላሳ ስምንት ሺህ አምስት መቶ ሃያ አንድ ብር) ጣልቃ-ገብ ለከሳሽ  እንዲከፍል ተወስኗል፡፡

4. ተከሳሽ በክሱ ምክንያት ያወጣው ወጪና የደረሰ ኪሳራ ካለ የራሱን እንዲችል ተብሏል፡፡

# ት ዕ ዛ ዝ

- ከአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን የወንጀልና ትራፊክ አደጋ ምርመራ በወንጀል ምርመራ መዝገብ ቁጥር 1311/12 የመጣው የምርመራ መዝገብ እና ከተከሳሽ ባንክ የቀረቡት ኦርጅናል ሰነዶች በመጡበት አኳኋን ተመላሽ እንዲደረግ ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡
- በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ይግባኝ ከጠየቀ የመዝገቡ ግልባጭ ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የዳኛ ፊርማ አለበት፡፡